12



ለ፡- ሁሉም ሥራ ሂደቶች

ቁጥር፡ ስ/አ/ጽ/ቤት 245/09

ከ፡- ሥራ አስኪያጅ ጽ/ቤት
አ/አ/ቃ/ጉ/ቅ/ጽ/ቤት፣

ቀን፡ 15/03/09 ዓ.ም

ከህግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በቁጥር 5.2.0/414/09 በቀን 14/03/2009 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ቀረጥና ታክስ የተከፈለበት እቃ ሙሉ በሙሉ ወደ አገር ውስጥ ሳይገባ የቀረ በመሆኑ ለሚቀርብ የቀረጥና ታክስ ተመላሽ ጥያቄ በየትኛው የጉምሩክ አዋጅ ድንጋጌ ሊስተናገድ እንደሚገባ በተጠየቀው መሰረት የተላከውን የህግ አስተያየት የተገለፀበትን 2 ገጽ ደብዳቤ ኮፒ በዚህ ሽኚ ደብዳቤ የተላከ መሆኑን እየገለጽን በዚሁ አግባብ አገልግሎት እንዲሰጥ አሳውቃለሁ።

ከሰላምታ ጋር

ግልባጭ፡-

- ለም/ሥራ አስኪያጅ /ሞደርናይዜሽንና ኮርፖሬት ዘርፍ/
- ለም/ሥራ አስኪያጅ /የጉምሩክ ጉዳዮች ዘርፍ/

አ.አ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

[illegible] 20/3/09 16/3/09

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN REVENUES AND CUSTOMS AUTHORITY

ቁጥር 5.20/4/14/09
Ref. No
ቀን 14 ህዳር 2009
Date

በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
ለአ.አ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
**አዲስ አበባ**

ጉዳዩ:- **የህግ አስተያየት ስለመስጠት**

ቀረጥና ታክስ የተከፈለበት ዕቃ ሙሉ በሙሉ ወደ አገር ውስጥ ሳይገባ የቀረ በመሆኑ ለሚቀርብ የቀረጥና ታክስ ተመላሽ ጥያቄ በየትኛው የጉምሩክ አዋጅ ድንጋጌ ሊስተናገድ እንደሚገባ እንዲሁም ጥያቄው የሚቀርብበት የጊዜ ገደብ ምን መሆን እንዳለበት የህግ ማብራሪያ እንዲሰጥበት በቁጥር አቃጉ02/አ/54/647 ጥቅምት 19 ቀን 2009ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ ተጠይቋል።

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/08 በምእራፍ አራት ስለቀረጥ፣ ታክስና አገልግሎት ክፍያዎች በተደነገገው ሥር በአንቀጽ 109 በማናቸውም የገቢ ወይም የወጪ እቃዎች ላይ ቀረጥና ታክስ እንደሚከፈል በግልጽ ተደንግጓል።ይሁን እንጂ ለዚህ ጥያቄ መነሻ በሆነው ጉዳይ ቀረጥና ታክስ የተከፈለበት ዕቃ ሙሉ በሙሉ ወደ አገር ውስጥ ሳይገባ የቀረ መሆኑ ተረጋግጧል። ስለሆነም ዕቃው ወደ አገር እስካልገባ ድረስ ቀረጥና ታክስ ሊከፈልበት አይችልም። የተከፈለ ቀረጥና ታክስ ካለም ተመላሽ መሆን ይኖርበታል።

በአዋጁ ቀረጥና ታክስ የተከፈለበት ዕቃ ሙሉ በሙሉ ወደ አገር ውስጥ ሳይገባ ሲቀር የሚቀርብ የቀረጥና ታክስ ተመላሽ ጥያቄም ሆነ ጥያቄው የሚቀርብበትን የጊዜ ገደብ የሚያስቀምጥ ድንጋጌ የለም። ለዚህም ምክንያቱ ከላይ በተገለጸው አንቀጽ መሰረት ቀረጥና


ስ.ቁ / Tel.. 011 662 98 00
ፋክስ / Fax: 011 662 99 06
ኢሜል / Email: erca@ethionet.et
ድረ ገጽ / Website: www.erca.gov.et
ፖ.ሣ.ቁ / P.O.Box: 2559
አዲስ አበባ-ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

ታክስ የመክፈል ግዴታ የተጣለው በማናቸውም የገቢ ወይም የወጪ እቃዎች ላይ እንጂ ወደ አገር ባልገባ ገቢ ዕቃ ላይ ወይም ከአገር ባልወጣ ወጪ ዕቃ ላይ ባለመሆኑ ነው፡፡

ሌላው በእንዲህ ዓይነት ጉዳይ የቀረጥና ታክስ ተመላሽ ጥያቄው የሚቀርብበት የጊዜ ገደብ በአዋጁ ያልተሸፈነ በመሆኑ የተመላሽ ጥያቄው አላግባብ ከመበልጸግ (Un Lawful enrichment) ጋር የሚያያዝ በመሆኑ የመብት ጥያቄ የሚቀርብበት ጊዜ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1845 መሰረት እስከ 10 ዓመት ድረስ በይርጋ ቀሪ የሚሆን አይደለም፡፡

ሲጠቃለል ቀረጥና ታክስ የተከፈለበት ዕቃ ሙሉ በሙሉ ወደ አገር ውስጥ ባለመግባቱ የሚሰበሰብ ቀረጥና ታክስ የማይኖር መሆኑን እንዲሁም የተከፈለ ቀረጥና ታክስ ካለም ተመላሽ መሆን ይኖርበታል፡፡ ስለሆነም ለዕቃው የተከፈለው የውጭ ምንዛሬ ተመላሽ መደረጉ ተረጋግጦ ወደ አገር ውስጥ ባልገባው በዚህ ዕቃ ላይ የተያዘ የቀረጥና ታክስ ዲፖዚት ወይም የተከፈለ ቀረጥና ታክስ ካለ ለአመልካቹ ሊመለስላቸው ይገባል በማለት አስተያየታችንን እናቀርባለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopian Revenues and Customs Authority

በለጠ አህመድ
የህግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

ግልባጭ፣
- ለህግ ምክርና አስተያየት ቡድን
- ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን